ከአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ሕፃናትን እየታደገ ያለው አለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

**ዳንኤል ዘነበ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ በየሦስት ደቂቃ ከከንፈርና ከላንቃ መሰንጠቅ ጋር አንድ ሕፃን እንደሚወለድ መረጃዎች ያሳያሉ። በአንፃሩ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአምስት ደቂቃ አንድ የከንፈርና ላንቃ ቀዶ ሕክምና የሚሠራ ቢሆንም፤ የላንቃ መሰንጠቅ ያለባቸው 60 ከመቶ የሚጠጉ ሕፃናት ሕክምና ሳያገኙ እንደሚሞቱ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም ከከንፈርና ላንቃ ጤና ችግር ስፋት አንፃር እየተደረገ ያለው የቀዶ ሕክምና እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቁማል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያም ቢሆን በቂ ልየታዎችና መረጃዎች ስለሌሉ እንጂ ይህ ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ ነው። ከከንፈርና ላንቃ ጤና ችግር ጋር የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር ከፍተኛ እንደሚሆንም ይገመታል።

የከንፈርና የላንቃ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጥ በወላጆች በኩል ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆንና አገልግሎቱ በአብዛኛው በረድዔት ድርጅቶች የሚሰጥና ውስን መሆን ደግሞ የታሰበውን ሕፃናት ቁጥር ያህል በቀዶ ሕክምና ተደራሽ ማድረግ አይቻልም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ተቋማት ሌት ተቀን በጉዳዩ ላይ እንደሚሠሩ እሙን ነው። እነዚህ መካከል ደግሞ አለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አንዱ ሲሆን፤ ባለፉት 15 ዓመታት በከንፈርና ላንቃ መሰንጠቅ ቀዶ ሕክምና ተደራሽ በመሆን የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕፃናትን ፈገግታ ሲመልስ ቆይቷል። እኛም በዛሬ እትማችን ይህንኑ ጉዳይ የምናዳስስ ይሆናል።

በአለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ሕክምና ክፍል ኃላፊ ዶክተር መክሊት ብርሃኔ ደግሞ ሙሉ መረጃውን የሰጡን ስፔሻሊስት ናቸው። በተለይም ስለከንፈር እና የላንቃ መሰንጠቅ ችግር በስፋት አብራርተውልናል እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል።

**የችግሩ መንስዔና ጉዳቱ**

የከንፈር እና የላንቃ መሰንጠቅ ችግር በእርግዝና ወቅት የሚከሰትና ሕጻናት ሲወለዱ የሚያጋጥማቸው ነው። ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን በሁለት እጥፍ የሚያጠቃ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ ችግሩ ያለባቸው ሰዎች የመስማት፣ የጆሮ መቁሰል እና የጥርስ ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። የከንፈር እና የላንቃ መሰንጠቅ መከሰት የተለያዩ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን፤ በዋናነት የከንፈር እና የላንቃ መሰንጠቅ የሚመጣው ከዘር እና ከአካባቢው ተፅዕኖ እንደሆነ ይታመናል።

የአንድ ሕፃን ወላጆች አንዱ ወይም ሁለቱ የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ካለባቸው አዲስ በሚወለድ ሕጻን ላይ ይህ ችግር የመከሰት ዕድሉ ሰፊ ነው። ሌላው ምክንያት ሊሆን የሚችለው እናት በእርግዝና ጊዜ የምትወስደው መድኃኒት ሲሆን፣ ከዚህም ሌላ ሕጻኑ በማኅጸን ውስጥ በነበረበት ጊዜ ለቫይረስ ወይም ለአደገኛ ኬሚካል የተጋለጠ ከሆነ ለከንፈር እና ለላንቃ መሰንጠቅ ችግር ሊጋለጥ ይችላል። በተጨማሪም የሚያጨሱ እና የስኳር በሽታ ያለባቸው ሴቶች የሚወልዷቸው ልጆች ለዚህ ጉዳት የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ነው። ስለዚህ የስኳር በሽታ ያለባቸው ሴቶች ለማርገዝ ከማቀዳቸው በፊት ከግል የጤና ባለሙያቸው ጋር መወያየት ይጠበቅባቸዋል።

**በሀገራችን የሕክምናው ተደራሽነትና የሆስፒታሉ ሚና**

የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ችግር ዓለም አቀፋዊ ቢሆንም በአፍሪካ ካለው ዝቅተኛ ኢኮኖሚ እና የሕክምና ተደራሽነት አንፃር ይበልጥ ጎልቶ ይታያል። በኢትዮጵያም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት ከከንፈርና ከላንቃ መሰንጠቅ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይገጥሟቸዋል። ችግሩ በደምብ ታውቆ የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት መሰጠት የተጀመረውም ካለፉት አስራ አምስት ዓመታት ወዲህ ነው።

በሀገራችን የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ያለባቸው ሕፃናት ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም፤ የሕክምናው ተደራሽነት ግን የቁጥሩን ያህል አይደለም። ስለበሽታው ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆንም በርካታ ተግዳሮቶችን ፈጥረዋል። አብዛኛው የሕፃናቱ ወላጆች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው መሆኑ እና ስለሕክምናው በቂ ግንዛቤ አለመኖሩ ሕፃናቱ የአመጋገብ እና የመጥባት ችግር እንዲያጋጥማቸው ያደርጋል። ይህም ችግሩ ያለባቸው ሕፃናት በኢንፌክሽንና ሌሎች መሰል ችግሮች እንዲሰቃዩ፤ ባስ ሲልም ከእነዚህ ችግሮች ጋር በተያያዘ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ሕይወታቸው እንደሚያልፍ ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ ለባለፉት አስራ አምስት ዓመታት አለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ሕክምና በመስጠት ብዙ ሺህዎችን ታድጓል።

አለርት ሆስፒታል በአሁኑ ወቅትም በዓመት ከ50 በላይ ሕጻናት በቀዶ ሕክምና እያዳነ ይገኛል። ይህም በቂ እንዳልሆነ በማመን ሕክምናውን ተደራሽ ለማድረግ «ስማይል ትሬን» ከተሰኘ ዓለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በመሆን እየሠራ ይገኛል። በ2015 ዓ.ም በዚሁ አጋር ድርጅት ድጋፍ የአለርት ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሕፃናት የላንቃ እና የከንፈር መሰንጠቅ የቀዶ ሕክምና መስጫ ማዕከል ገንብቷል። በሕፃናት የላንቃ እና የከንፈር መሰንጠቅ የቀዶ ሕክምና መስጫ ማዕከሉም በዓመት ከ50 በላይ ሕፃናት ቀዶ ሕክምና ይደረግላቸዋል። በ2016 ዓ.ም በቁጥር ከሃምሳ እስከ ሰማኒያ ሕፃናት በማዕከሉ ቀዶ ሕክምና ተደርጎላቸዋልም። አሁን ላይ በማዕከሉ የቀዶ ሕክምና የሚደረግላቸው ከስድስት ወር በላይ የሆኑ ሕጻናት ሲሆኑ፤ ወላጆች በሕክምና ተቋማት እንዲወልዱ በማድረግ ሕፃናቱ ስድስት ወር ሲሞላቸው ሕክምና እንዲደረግላቸው እየተሞከረ ነው። ይህም በልጆች ላይ የሚደርሰውን አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳት ይቀንሳል።

**የማዕከሉ መገንባት ያስው ፋይዳ**

የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ችግር የሚያጋጥማቸው ሕፃናት የተሟላ የከንፈርና የላንቃ ሕክምና ያስፈልጋቸዋል። ይህም ከቀዶ ሕክምናው በተጨማሪ፤ የሥነ ምግብ አገልግሎትም እንዲሁ ለሕፃናቱ ያስፈልጋል። ሕፃናቱ ላንቃቸው ክፍት ሆኖ ሲዘጋ ወይም በቀዶ ሕክምና ወደነበረበት ሲመለስ ንግግራቸው በግልፅ ስለማይሰማ የንግግር ሕክምናም ያስፈልጋቸዋል። ላንቃቸው ክፍተት ስለነበረው የጥርሳቸው አቀማመጥ ትክክል አይሆንም። ስለዚህ የጥርስ ሕክምናም እንዲሁ ሊያገኙ ይገባል። እንዲሁም ከእንዲህ አይነት መሰል አፈጣጠር ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች በማኅበረሰቡ ዘንድ መገለልና መድሎም ጭምር ስለሚያስከትሉ የማኅበራዊና የሥነ ልቦና ሕክምናም ጭምር ይፈልጋሉ። ስለዚህ ቀዶ ሕክምናው ብቻ በቂ አይደለም ማለት ነው። ከዚህ አንፃር ማዕከሉ መጀመሩ ከሕክምናው ባሻገር እንደ የሥነ ምግብ ሕክምና መስጠት እንዲቻል አድርጓል። በተጨማሪም የንግግር ክህሎት፣ የጥርስ አቀማመጥ ሕክምና እንዲሁም የሥነ ልቦና ሕክምናም መስጠት አስችሏል።

በሕክምናው በኩል ከሚታዩ ችግሮች መካከል አንዱ ሕክምናው በአብዛኛው አዲስ አበባ የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በገጠር አካባቢዎች የሚገኙና የዚህ ችግር ሰለባ ለሆኑት ተደራሽ መሆን አለመቻሉ ነው። በዚህ የተነሳ በወላጅም ሆነ በታካሚው በኩል የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ጫናዎች ይኖራሉ። ወላጆችም ካለባቸው ችግር የተነሳ ወደ ከተማ መጥተው ልጆቻቸውን የማሳከም እቅድ የላቸውም። ከዚህ አንፃር አለርት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለእነዚህ በገጠር አካባቢ ላሉና ለሕክምናው ተደራሽ ላልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የትራንስፖርት፣ የምግብና የሕክምና ወጪ ችሎ በአዲስ አበባ ሕክምናውን እንዲያገኙ ያደርጋል። በዚህም በተወሰነ መልኩ ለእነዚህ ዜጎች የሕክምና በር ከፍቷል።



ዶክተር መክሊት ብርሃኔ

**በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

በኢትዮጵያ ከላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ ጋር የተያያዘ ችግር ያለባቸው ሕፃናት ቁጥር ከፍተኛ ነው ተብሎ ይገመታል። ካለው ከፍተኛ ቁጥር አንፃር ግን በሚፈለገው ልክ የቀዶ ሕክምና አገልግሎቱን ለማግኘት ሕፃናት ወደ ጤና ተቋማት አይመጡም። እናቶችም በዚህ ችግር ምክንያት ከፍተኛ ጫና ውስጥ ይገባሉ። የከንፈርና ላንቃ መሰንጠቅ በሕክምና የሚስተካከል አይመስላቸውም። ጡት ማጥባት አይችሉም፤ ልጃቸውን መመገብ ይቸገራሉ። ልጆቻቸው ትንታ ያጋጥማቸዋል። የሚፈልጉትን መጠን ያህል ጡት ማጥባትም ያስቸግራቸዋል። ከዚህ አንፃር የሕፃኑ ክብደት ይቀንሳል። በዚህና ተያያዥ ምክንያቶች የበርካታ ሕፃናት ሕይወት ያልፋል።

ስለዚህ ከመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ብሎም ከሚዲያዎች ጋር መሥራት ዋነኛ ጉዳይ ሊሆን ይገባል። ይህ ሥራ የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ችግር ያለባቸው ሕፃናትን አስቀድሞ በመለየት ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ያስችላልና ሁሉም ልብ ሊለው ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ሕክምናው እንዳለና የት እንደሚሰጥ ለወላጆች መረጃ መስጠት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ከተቻለ ሕፃናት ሳይጎዱና የሰውነታቸው ክብደት ሳይቀንስ በትክክለኛው ሰዓት ቀዶ ሕክምና አገልግሎቱን አግኝተው ጤናማ ሆነው ሊያድጉ ይችላሉ። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዓለም አቀፍ ደረጃ በየሦስት ደቂቃ ከከንፈርና ከላንቃ መሰንጠቅ ጋር በተያያዘ አንድ ሕጻን ይወለዳል። በአንፃሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአምስት ደቂቃ አንድ የከንፈርና ላንቃ ቀዶ ሕክምና ይሠራል። ከችግሩ ስፋት አንፃር ብዙ ቀዶ ሕክምናዎችን መሥራት ይጠበቃል። ቀዶ ሕክምናውን ያላገኙና አገልግሎቱን የሚጠባበቁትን ሕፃናትንም መለየት ተገቢ ነው።